| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | ዐምደኛ ፡ ጽሑፍ ፤ "ዜና ፡ ስሌት ፡፡ " |
| ርእስ ፤ | *"5G ፡ ወይም ፡ 5 ኛ ፡ ትውልድ ፡ እና ፡ እኸል-ገብ ፡ ኢንተርኔት ፡፡ "* |
| ደራሲ ፤ | *"ሥልጡንሕዝብና"* ፡ መዜንው ፡፡ |
| ዕለት ፤ | ነሐሴ ፡ 2011 ፡ ዓ.ም. ፡፡ |
| ዝግጅት ፤ | ፍጹም ፡፡ |
| መጽሔት ፤ | *"ሥልጡንሕዝብና"* ፡ መዜንው ፥ ቍ.2011-003 ፡፡ |
| ማስታወሻ ፤ | |
| ማሳሰቢያ ፤ | |

# ዜና ፡ ስሌት ፡፡

Computing News | Nouvelles d'informatique | اخبار العقل

## 5G ፡ ወይም ፡ 5 ኛ ፡ ትውልድ ፡ እና ፡ እኸል-ገብ ፡ ኢንተርኔት ፡፡

---

**የአንከርት ፡ ስልክ ፡ ኪነት** ፡ (mobile phone technology) ፡ በሠላሳ ፡ ዓመታት ፡ ታሪኩ ፥ ዘንድሮ ፡ 5 ኛ ፡ ትውልዱን ፡ ወልዷል ፡፡ ወላጅ ፡ ከልጆቹ ፡ የሚለየውን ፡ ያኽል ፡ ይሀ ፡ 5 ኛው ፡ የኪነት ፡ ትውልድ ፡ ከቀደሙት ፡ 4G ፡ እና ፡ 3G ፡ ... ፡ ይለያል ፡፡

5G ፡ ከሚያመጣቸው ፡ መሻሻሎች ፡ ውስጥ ፦

- ፍጥነት ፤ ሽቦ-አልቦ ፡ (wireless) ፡ የሚተላለፈው ፡ የስልክ ፡ መልክት ፡ መጠን ፡ እስከ ፡ 20 ፡ Gbps ፡ (Giga bits per second ፥ ወይም ፡ 20 ፡ ቢልዮን ፡ ኹለትዮ ፡ ንምራ ፡ በካልኢት) ፡ ይደርሳል ፡ (በ 4G ፡ ከ 1Gbps ፡ አያልፍም) ፡፡
- የሥርጭት ፡ ዝግየታው ፡ (latency ው) ፡ ካ 1 ፡ ms ፡ (milliseconds ፡ ወይም ፡ ካ 1 ፡ ካልኢት-ሺኛ) ፡ አይበልጥም ፡፡
- የበለጠ ፡ ፈሰሳ ፡ (bandwidth) ፡ እና ፡ የተሻሻለ ፡ የቀጠጥና ፡ ኪነት ፡ (antenna technology) ፡ ስለሚኖር ፥ በ 5G ፡ የሚዘዋወረው ፡ ልቅም ፡ (data) ፡ መጠን ፡ የላቀ ፡ ይኾናል ፡፡
- 5G ፡ የቀለጠፈ ፡ የመርበብት ፡ አስተዳደር ፡ (network management) ፡ ስለሚኖረውም ፥ ከእውነተኛው ፡ 5G ፡ መርበብት ፡ ጋራ ፡ ሌሎች ፡ የመርበብት ፡ ክፍለቶችን ፡ ለመፍጠርና ፥ ለእያንዳንዱ ፡ የተለየ ፡ አስተዳደር ፡ ለመመደብ ፡ ያስችላል ፡፡

ሽቦ-አልቦ ፡ መርበብት ፡ የሚዘረጋው ፡ በማቄሪያ ፡ (cell) ፡ ማማ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ ሥርጭቱ ፡ ከማቄሪያ ፡ እማቄሪያ ፡ በሚቀባበል ፡ የምዕዛር ፡ (radio) ፡ ሞገድ ፡ (wave) ፡ ይከናወናል ፡፡ ኾኖም ፥ ለ 4G ፡ ረኸሮም ፡ የማቄሪያ ፡ ማማ ፡ ሩቅ ፡ ለሩቅ ፡ ያስፈለገውን ፡ ያኽል ፥ ለ 5G ፡ ደግሞ ፡ ቅርብ ፡ ለቅርብ ፡ የተተከሉ ፡ አነስተኛዎች ፡ ማማዎች ፡ ይበቁታል ፥ ምክንያቱም ፥ እጅግ ፡ ፈጣን ፡ ሥርጭት ፡ እንዲኖረው ፡ ብዙ ፡ ርቀት ፡ በማይዘልቅ ፡ በከፍተኛ ፡ የምዕዛር ፡ ብዛት ፡ (frequency) ፡ ይሠራል ፡፡ ይሀ ፡ ኹኔታ ፡ ግን ፡ 5G ን ፡ ለልዩ ፡ ልዩ ፡ የአካልና ፡ የአየር ፡ ጠባይ ፡ መሰናክሎች ፡ ይዳርገዋል ፡፡

ባኹኑ ፡ ሰዓት ፥ 5G ፡ ዐሥር ፡ እማይሞሉ ፡ አገሮች ፡ ውስጥ ፡ ባነስተኛ ፡ ደረጃ ፡ ተዘርግቷል ፤ በመላ ፡ ዓለም ፡ እስኪዘረጋ ፡ 10 ፡ ዓመት ፡ ይፈጃል ፡ ተብሎ ፡ ይገመታል ፡፡

5G ፥ በማሠራጫ ፡ ፈጣንነቱ ፣ በፈሰሳ ፡ ብልጫውና ፡ በመለስተኛ ፡ ዝግየታው ፡ ላዳዲስ ፡ ኪነቶች ፡ አዋዋል ፡ ይመቻል ፡፡ ከነዚህ ፡ ዐዳዲስ ፡ ኪነቶች ፡ ውስጥ ፥ ነጂ-አልቦ ፡ መንንገሮ ፣ በ"ሮቦት" ፡ የታገዘ ፡ የርቀት ፡ ሥራ ፡ ይገኙበታል ፡፡

በተለይ ፡ ደግሞ ፥ ባኹኑ ፡ ሰዓት ፡ እጅግ ፡ ለሚስፋፋው ፡ *"እኸል-ገብ ፡ መርበብት"* ፡ ወይም ፡ *"Internet of Things"* ፡ በር ፡ ይከፍትለታል ፡፡ እንደ ፡ ልብስ ፡ ማጠቢያ ፣ ማቀዝቀዣ ፣ መኪና ፣ ስልክ ፣ የቤት ፡ ማሞቂያ ፣ ... ፡ ያሉ ፡ መሣሪያዎች ፥ እንደ ፡ ሰዉ ፡ ኹሉ ፥ የ IP [1] ፡ አድራሻ ፡ ኖሯቸው ፥ ርስ ፡ በርሳቸውም ፡ ኾነ ፡ ካንዳች ፡ ማእከል ፡ ጋራ ፡ በ 5G ፡ መርበብት ፡ አማካይነት ፥ *"ደከመኝ ፤ ሰለቸኝ"* ፡ ሳይሉ ፥ መረጃን ፡ በማቀበል ፣ መቀባበልና ፡ ለማቀባበል ፡ አካባቢውን ፥ ለደኅናም ፡ ኾነ ፡ ለሌላ ፥ መቈጣጠር ፡ ያስችላሉ ፡፡

እውነት ፡ ለመናገር ፥ 5G ፡ የሚያስችለው ፡

---

1 IP ፡ ወይም ፡ Internet Protocol ፤ ከምንጩ ፡ እስከ ፡ መድረሻው ፡ የመረጃን ፡ የኢንተርኔት ፡ ፍናዌ ፡ ወይም ፡ አላላክ ፡ ዝርዝር ፡ የሚቈጣጠር ፡ ሥርዐት ፡፡


©ኢ.ሀ.ሥ. አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ፡፡

ነገር ፡ ኹሉ ፡ አስቀድሞ ፡ ተዘርዝሮ ፡ የሚታወቅ ፡ አይደለም ።  ገና ፡ ማንም ፡ ዛሬ ፡ ያላሰባቸው ፡ ብዙ ፡ አዋዋሎች ፡ ስለሚኖሩት ፥  በተለይ ፡ ኀያላን ፡ መንግሥታት ፡ ለየብቻቸው ፡ ጠቅልሎ ፡ የመያዝ ፡ ፍላጎትን ፡ ካኹኑ ፡ ማሳየት ፡ ዠምረዋል ።

የሰው ፡ ልጅ ፡ ካልተጠነቀቀ ፥  ምናልባት ፡ ሳያውቀው ፡ ነጻነቱንም ፡ በመርበብት ፡ ሊነጠቅ ፡ ይችላልና ፥  ዘው ፡ ዘው ፡ ከማለቱ ፡ በፊት ፡ ለነጻነቱ ፡ በቂ ፡ ዋስትና ፡ መኖሩን ፡ አስቀድሞ ፡ ማረጋገጥ ፡ ይገባዋል ❖


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።